ቀን ----------

<u>የስራ ውል ስምምነት</u>

ውል ሰጪ ----------

አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12

ውል ተቀባይ ----------

አድራሻ አዲስ አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 7

ይህ ስራ ስምምነት ውል ዛሬ ቀን 2/7/2009 ዓ.ም ከዚህ በኋላ ውል ሰጪ ተብሎ በሚጠሩት በአቶ ---------- እና ውል ተቀባይ ተብሎ በሚጠሩት በአቶ ደገፉ ወልዴ መካከል የተደረገ የግንባታ ስራ ከትትልና ቁጥጥር ስራ ውል ነው።

<u>አንቀጽ 1 የውሉ አላማ</u>

1.1 በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚሰራ የአቶ ---------- የመኖሪያ ቤት ከመሰረት ወለል አንስቶ እስከ 2 ኛ ፎቅ ድረስ ያለውን አጠቃላይ የብኬት ግንባታ የልስን ስራ ጥራት ለመከታተልና ለመቆጣጠር ነው።

<u>አንቀጽ 2 ውል ሰጪ ግዴታዎች</u>

2.1 የግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለግንበኛ ለለሳኝ በወቅቱ ማቅረብ

2.2 ውል ሰጪ ለውል ተቀባይ ለግንባታና ለልስን ስራ ክትትል ብር 25,000.00/ሀያ አምስት ሺህ ብር ለመክፈል ተስማምቷል ለግንባታ ስራ ብር 10,000.00/ አስር ሺህ ብር ለልስን ስራ 15,000.00/ አስራ አምስት ሺህ ብር/ ለመክፈል ሲሆን አከፋፈሉም ለግንባታ ስራ ውል ከተገባበት ቀን አንስቶ እስከ 15 ቀን ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/ ይከፍላሉ ቀሪውን 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/ የግንባታው ስራ ሙሉ በሙሉ እንደተጠናቀቀ ይከፍላሉ።

የልስን ስራ የውስጥ ግድግዳ ስላብ ልስን ሙሌት እንደተጠናቀቀ ብር 10,000.00/ አስር ሺህ ብር ይከፍላሉ ቀሪውን ክፍያ ውጭ ግድግዳ ፈኖና የጠርዝ ስራ እንደተጠናቀቀ ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/ ይከፍላሉ።

<u>አንቀጽ ሶስት የውል ተቀባይ ግዴታዎች</u>

3.1 ውል ተቀባይ የልስን ስራ ውል ሰጪ የሚያቀርቡትን ባለሙያዎች ስራውን በአግባቡ እንዲሰሩ የመመረት፣ የመከታተል ፣ ጥራቱን የጠበቀ ስራ የማሰራት ኃላፊነት አለባቸው

3.2 ውል ተቀባይ የማቴሪያል ጥራት መቆጣጠር የአሸዋና የሲሚንቶ ሬሾ መቆጣጠር ስራውን በፕላን (በንድፉ) መሰረት ማሰራት እና የማቴሪያል ጥራት መቆጣጠር

3.3 ውል ተቀባይ በሳምንት ሶስት ቀን በሳይት ላይ በመገኘት ስራውን በአግባቡ ማየትና መከታተል ለግንበኛም ሆነ ለለሳኝ የስራ ትዕዛዝ መስጠት ባለሙያዎች የሰሩት ስራ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ እና ግንበኛ ለሳኝ የሰሩትን ስራ ልኬት መውሰድና የክፍያ ሰነድ ማዘጋጀት

<u>አንቀጽ 4 ተጠያቂነትና ኃላፊነት</u>

4.1 ውል ሰጪና ውል ተቀባይ ሁለቱም ወገን ይህን ውል የመፈጸም ኃላፊነት አለባቸው የስራ ውል ስምምነት ለማፍረስ የሞከረ ወገን ቢኖር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005(1) 1889/1890 በሚያዘው መሰረት ለመንግስት ብር 1,000.00/አንድሺህ ብር/ ውሉን ላከበረው ወገን ብር 1,000.00/አንድሺህ ብር/ ከፍሎ ውሉም በህግ ፊት የጸና ይሆናል።

ውል ሰጪ ስምና ፊርማ ምስክሮች ውል ተቀባይ ስምና ፊርማ

---------- 1 ---------- ----------

2 ----------